ማወቅ ያለብዎት ነገር

የ COVID-19 ምርመራ

1 ምርመራው እንዴት ይካሄዳል?

የ COVID-19 ምልክቶች ካለብዎት ወይንም COVID-19 ካለዉ ሰዉ ጋር በቅርብ ከተገናኙ ምርምራ ማድረግ አለብዎት። ምርመራ ማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች መጀመሪያ ሃኪማቸዉን ማነጋገር አለባቸዉ።

ሃኪም ይጎብኙ

ሰዎች ለCOVID-19 ምልክቶች በሃኪማቸዉ በአካል ወይንም በስልክ ይገመገማሉ። በዋሽንግተን የጤና ቢሮ የምርመራ መመሪያ መሠረት ሃኪምዎ ምርመራ የሚያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል።

የአፍንጫ ናሙና ይወሰዳል

አገልግሎት ሰጪው የCOVID-19 ምርመራ አስፈላጊ እንደሆነ ቢወስን፤ አገልግሎት ሰጪው የአፍንጫ ናሙና ይወስዳል ወይም ታካሚው በራሱ ናሙናውን እንዴት እንደሚወስድ ምሪት ይሰጣል።





ናሙናው ወደ ላብራቶሪ ይላካል

የመመርመሪያው መሳሪያ ከናሙናው ጋር ለምዘና ወደ ላብራቶሪ ይላካል።

የላብራቶሪ ውጤት ለታካሚ ይመለሳል።

የምርመራው ውጤት ፖዝቲቭ ከሆነ፣ የምርመራ ውጤቶቹ ለ Public Health (ማህበረሰብ ጤና) - Seattle & King County ይገለጻሉ።

2 ምርመራ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የ COVID-19 ምልክቶች ያለበት ወይንም COVID-19 ካለዉ ሰዉ ጋር በቅርብ የተገናኘ ማንኛዉም ሰዉ ወዲያዉ መመርመር አለበት። ምርመራዉን እንዴት እንደሚያገኙ የሚወሰነዉ በማንነትዎ ነዉ። ቅድሚያ የሚሰጣቸዉ ቡድኖች፣ እንደ የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎች፣ የጤና ሠራተኞች፣ እና በሼልተርና እንዲሁም የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ተቋማት ዉስጥ ተሰባስበው የሚኖሩ ካለባቸዉ ከፍተኛ ስጋት የተነሳ ከጠቅላላ ማህበረሰቡ ለየት ያለ ምርመራ የማግኘት መንገድ አላቸዉ።

የመጀመሪያ ምላሽ ሰጪዎች

እንደ ፖሊስ እና ድንገተኛ የህክምና ሠራተኞች ያሉት የ COVID-19 ምልክቶች የሚታይባቸው ከሆነ ከጤና መኮንናቸው ጋር መነጋገር አለባቸው። የመጀመሪያ ምላሽ ሰጪዎች ወደ ስራ በቶሎ እንዲመለሱ ለቀልጣፋ ምርመራ ልዩ አደረጃጀት ይዘጋጃል።



የጤና ባለሙያዎች

የጤና ባለሙያዎች የ COVID-19 ምልክቶች የሚታይባቸው ከሆነ ምርመራውን ሊያቀርቡላቸው ከሚገባ የሰራተኛ ጤና አገልግሎት ወይም የጤና እንክብካቤ ሰጪያቸው ጋር መነጋገር አለባቸው።

በተከማቹ ስፍራዎች የሚሰሩ ወይም የሚኖሩ ሰዎች

ከፍተኛ ተጋላጭነት ባላቸው በተከማቸ ስፍራዎች እንደ ረጅም ጊዜ የእንክብካቤ ጣቢያ ወይም የቤት አልባዎች አገልግሎት ሰጪ ቦታዎች ውስጥ ለሚኖሩ እና ለሚሰሩ ሰዎች የ COVID-19 ምልክቶች የሚታይባቸውን ግለሰቦች ለመርዳት ምርመራ እና ድጋፍ እንዲያገኙ የጤና አገልገሎቶችን ሰጥተዋል።

የታመሙ ሰዎች

ከነዚህ ቡድኖች ካንዱ ዉስጥ የማይመደቡ ከሆነና የ COVID-19 ምልክቶች ካለብዎት ወይንም COVID-19 ካለዉ ሰዉ ጋር በቅርብ ከተገናኙ እባክዎን ሃኪሞ ጋ ይደዉሉ። ምንም እንኳ ሃኪሞ ምርመራ የማያደርግ ቢሆንም ምልክቶችዎን ከርስዎ ጋር ሊወያይና ምርመራና እንክብካቤ እንድያገኙ ሊረዳዎች ይችላል።

ይህ ስዕላዊ መረጃ ሜይ 12 2020 የተሻሻለ ነዉ። መረጃ ሊቀየር ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ የCOVID ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ፡
https://kingcounty.gov/depts/health/covid-19/languages/amharic.aspx

ስለ COVID-19 ጥያቄ ካለዎት ለ King County ኮሮና ቫይረስ የጥሪ ማዕከል ተርጓሚዎች ይገኛሉ። ተርጓሚ ካስፈለገዎት በ 206-477-3977 ይደውሉ።

Public Health
Seattle & King County